# ፀረ-ሙስና

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 41 ግንቦት 15 /2018 ዓ.ም


## በውስጥ ገፆች


ሙስናና ለአገልግሎት እጅ መንሻ የሚጠይቁትን ለማጋለጥ፥ በሚዲያ በግልፅ ተጠያቂ የማድረግ፤ አስተዳደራዊና በወንጀል በህግ ተጠያቂነትን የማስፈን ስራዎች እየሰራን ነው - ከንቲባ አዳነች አቤቤ
ገጽ 2

የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሕጋዊ ግዴታ ብቻ ሳይሆን የተቋሙ መለያና ዋና መሠረት ነው - አቶ ፀሐይ ሽፈራው
ገጽ 4

በስህተት ወደ ባንክ አካውንቱ የገባውን ገንዘብ ተመላሽ ያደረገው የፖሊስ አመራር በባንኩ ተመሰገነ
ገጽ 9


## ላባችንን አንጠፍጥፈን ካልሠራን እና የሌብነትን አረም ካላስወገድን ለውጥ አይመጣም - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)







ላባችንን አንጠፍጥፈን ካልሠራን እና የሌብነትን አረም ካላስወገድን ለውጥ አይመጣም ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ይህን ያሉት የገላን ጉራ ኢንዱስትሪ ፓርክ በተመረቀበት ወቅት ነው።

የገላን ጉራ ኢንዱስትሪ ፓርክ መመረቅ ተራ የህንፃዎች ስብስብ ሳይሆን የኢትዮጵያን የከተማነት መልክዓ-ምድር በአጭር ጊዜ የመቀየር ትልቅ ማሳያ ነው። የዛሬ ሁለት ዓመት መኪና የማይደርስበት ገጠር የነበረው ይሄው ቀጠና ዛሬ በዘመናዊ አስፓልት፣ በቤት ግንባታ እና በአረንጓዴ መናፈሻዎች ደምቆ የአዲስ አበባ አዲስ የኢኮኖሚ ማዕከል ሆኗል ብለዋል። ሆኖም በልማት ሥራዎች መካከል የሚስተዋለው የሌብነት አረም ፈጥኖ ሊወገድ ይገባል።

ሌብነት ካለ የልማት ሥራው እንደማያዋጣ እና ሌቦች ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ያስጠነቀቁት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ሰዎችን ሳይከፋፍሉ ሁሉንም በአንድነት አቅፎ በመያዝ ለኢትዮጵያ ብልጽግና በጋራ እንስራ ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በመልዕክታቸው፥ የተጀመረው ትልቅ ጉዞ እንዳይደናቀፍ በሥራው ውስጥ የሚዘሩ “የሌብነት አረሞች” በአስቸኳይ ሊነቀሉ እንደሚገባ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል፡ ፡ሙስና የሀገርን ልፋት



## የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች ዘርፍ ተኮር ስልጠናዊ ውይይት አካሄዱ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን “የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ!” በሚል መሪ ቃል ከውጭ ጉዳይ ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ዘርፍ-ተኮር ስልጠናዊ ውይይት አካሂዷል። ስልጠናዊ ውይይቱ በዘርፉ የሚስተዋሉ ዋና ዋና የሙስና ሥጋት እና ተጋላጭነት መገለጫ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እና ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭት ማስተዳደር ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ትኩረት ያደረገ ነው።

በስልጠናዊ ውይይቱ የተገኙት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ ክቡር አቶ አዳም ተስፋዬ ለህዝብ ፈጣን እና ፍትሃዊ አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር ፍፁም እና ሥነምግባራዊ በሆነ መንገድ ማገልገል የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን ተናግረዋል። ሙስና በዲፕሎማሲ እና በአለም አቀፍ ግንኙነት ሀገራችንን ዋጋ የሚያስከፍል ክፉ ደዌ መሆኑንም አፅንኦት ሰጥተው ገልጸዋል። ሙስና የፍትሕ ስርዓትን እና የፖለቲካ ምህዳርን የሚያበላሽ፣ ተቋማትን የሚያጠፋና ሁሉንም ማህበረሰብ የሚጎዳ መሆኑን ጠቅሰው፥ በተለይም በአለም አቀፍ ደረጃ የመንግስትን ተዓማኒነት

ወደ ገጽ 2 የዞረ

**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!**

የውጭ ጉዳይ ዘርፍ... ከገጽ 1 የዞረ





የሚሸረሽርና ወዳጅነትን የሚያሳጣ እንዲሁም ብሔራዊ ጥቅምን የሚጎዳ መሆኑን አስምረውበታል።

አክለውም የፀረ-ሙስና ትግል የሁሉም ሰው ሥራ እና ኃላፊነት ቢሆንም፣ አመራሩ ግን በታማኝነት እና በቅንነት ኃላፊነቱን በመወጣት ለሌሎች ምሳሌ መሆን እንደሚኖርበት አሳስበዋል። ስልጠናው ለሥነምግባር ግንባታ ካለው ፋይዳ ባሻገር የሀገርን ሀብት በአግባቡ ከመጠቀምና ሃላፊነትን በታማኝነት ከመወጣት አንፃር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

በፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ገልጸው፥ አመራሮች እና ዲፕሎማቶች ይህንን ወደር የለሽ ሀገራዊ ተልዕኮ በሚወጡበት ጊዜ፣ ራሳቸውን ከሙስና እና ብልሹ አሰራር ከሚያጋልጡ ሁኔታዎች እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉና ሙያዊ ግንኙነቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ በሥነ-ምግባር ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲችሉ ስልጠናው ከፍተኛ ግንዛቤ እንደሚፈጥር ተናግረዋል። የስልጠናዊ ውይይቱ ተሳታፊዎች በጥቅም ግጭትና ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሰፊ ግንዛቤ እንዳገኙ የገለጹ ሲሆን፥ በመድረኩም ጥያቄዎች፣ አስተያየቶችና ሀሳቦች ተነስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

## በተቀናጀ የሙስና መከላከል ስልቶች ላይ ያተከረ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጠ





የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለዘርፎች ፎረም አመራሮች እና ለሥነ-ምግባርና ፀረሙስና ስራ አስፈፃሚዎች በተቀናጀ የሙስና መከላከል ስልቶች ላይ ያተከረ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ሰጥቷል፡ ፡ ሥልጠናውን ያስጀመሩት የኮሚሽኑ የሥነ-ምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ እንደገለፁት የሥልጠናው ዋና አላማ በተቀናጀ የሙስና መከላከል ስልቶች ላይ የእውቀት፣ ክህሎት እና ቁርጠኝነት ቁመና ተላብሳችሁ ስራዎቻችሁን መምራት የሚያስችላችሁን አቅም ለመገንባት ያለመ ነው ብለዋል።

አክለውም የፀረ-ሙስና ትግሉን ስኬታማና ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ አካላት ተቀናጅተው መስራት ይኖርባቸዋል። እነዚህ አካላትም የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች፣ ህግ፣ ለውጥ፣ የውስጥ ኦዲት እና የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን የስራ ክፍሎች እንዲሁም ዘርፎች እርስ በርሳቸው፣ ዘርፎች ከተጠሪ ተቋማት ጋር እና ዘርፎች ከኮሚሽኑ ጋር መቀናጀት እንዳለባቸው ጠቁመዋል። ይህ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስልት ውጤት እንዲያመጣ በዋናነት የተቋማት ሀላፊዎች በባለቤትነት ሊመሩት ይገባል፡ ፡ ለዚህም ውጤታማነት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ከኃለፊዎች ጋር በተናበበና ተግባቦት በተሞላበት መንፈስ ሆኖ መስራት እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

በመጨረሻም መከታተያ ክፍሎች የበጀት አመቱን እቅዳቸውን መለስ ብሎ በማየት ሙሉ በሙሉ፣ የተከናወኑ፣ በከፊል የተከናወኑ እና ምንም ያልተከናወኑትን በመለየት በቀጣይ ቀሪ ወርና ቀናት በፍጥነት ማሳካት እንዳለባቸው አቅጣጫ ሰጥተዋል። ሥልጠናውን የሰጡት የኮሚሽኑ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ስልጠና ዴስክ ሀላፊ የሆኑት አቶ ኪዳነ ምህረት እና የራሚስ ባንክ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ሀሰን ሙሀመድ ናቸው። አሰልጣኞቹ ከርዕሱ ጋር ተያያዥ ኬዞችን በማንሳት በዝርዝር ያስረዱ ሲሆን፥ በመከላከያ ስልቶቹ ላይ ተሞክሮዎችን ጭምር በማንሳት ተሳታፊዎች እንዲወያዩ በማድረግ ስልጠናውን አከናውነዋል።

የስልጠናው ተሳታፊዎችም በተቀናጀ የሙስና መከላከል ስልቶች ላይ ያተኮረ ሥልጠና መሰጠቱ ስራወቻችን ላይ ውጤታማ እንድንሆን ያስችለናል ብለዋል። ቅንጅታዊ አሰራሩን ውጤታማ ለማድረግ በየተቋማቱ የተፈቀዱ የመከታተያ ክፍል መዋቅሮችን በሰው ሀይል ማሟላት ያስፈልጋል ሲሉ አስተያየታቸውንም ሰጥተዋል።

## ሙስናና ለአገልግሎት እጅ መንሻ የሚጠይቁትን ለማጋለጥ፥ በሚዲያ በግልፅ ተጠያቂ የማድረግ፤ አስተዳደራዊና በወንጀል በህግ ተጠያቂነትን የማስፈን ስራዎች እየሰራን ነው - ከንቲባ አዳነች አቤቤ





ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ሚዲያ ፣ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት፤ በበጀት ዓመቱ በተግዳሮት ውስጥ የነበረው አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል የአዲስ መሶብ አንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎትን በስድስት ማዕከላት ተግባራዊ ማድረግ ችለናል ብለዋል። በዚህም 150 አገልግሎቶች ወደ መሶብ ዲጂታል አንድ ማዕከል በማስገባት ቀልጣፋና ፍትሐዊ አገልግሎት መስጠት ጀምረናል። በአጭር ጊዜ ውስጥም ቀሪ አምስት ማዕከላት ወደ ሥራ እንደሚገቡ ጠቁመዋል።

ሙስናና ለአገልግሎት እጅ መንሻ የሚጠይቁትን ለማጋለጥ፥ በሚዲያ በግልፅ ተጠያቂ የማድረግ፤ አስተዳደራዊና በወንጀል በህግ ተጠያቂነትን የማስፈን ስራዎች እየሰራን ነው። በበጀት ዓመቱ እስከ 9 ወር ድረስ ባለው የተያዙ ተጠርጣሪዎች 420 ሲሆን፥ አመራር 40፥ ባለሙያ 230፥ የተጠረጠሩበት ወንጀል ተጠቃሚ ሰዎች 150 ሲሆኑ ሁሉንም እንደየተሳትፎቸዉ ተጠያቂ ተደርገዋል ብለዋል። በተያዘ መረጃ፤ ጉቦ እና እጅ መንሻ መጠየቅ፤ አገልግሎት መስጠት ላይ እንቅፋት ሆኖ መቀጠሉም ከምክር ቤት አባል ተነስቷል።


ጉቦ ጠይቀው የተገኙት ላይም የሚወሰድባቸው እርምጃ እና የሚወሰኑ ውሳኔዎች ቀለል ያሉ ናቸው ተብሏል። ይህ መሆኑ ጉቦ ጠያቂዎቹ የበለጠ እየተደፋፈሩ እንደሆነና ቀጣቱ ሌሎችን ሊያስተምር እንዳልቻለ ተጠቅሷል። ይህንን ተግባር ለማስቀም ምን እየተሰራ እንደሆነም ጥያቄ ቀርቧል። ከምክር ቤት አባል ለተነሳው ጥያቄ የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች ምላሽ ሰጥተዋል።

በምላሻቸውም ችግሩ መኖሩን አምነው ይህንን ስር የሰደደውን ሌብነት ለማስቀም የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆኑን ጠቅሰዋል። ጥቆማዎች፣ ግምገማዎች እና የኦዲት ሪፖርቶችን በመንተራስ ችግሮቹን ለመፍተታ እየተሰራ ነው ብለዋል። ጉቦኝነት እና ሌብነት በከተማዋ እየተፈፀሙ ይገኛሉ ያሉት የስራ ሀላፊዎች፤ ባለሞያው እና አመራሩ "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" በሚል ብሒል ያደገ ስለሆነ ችግሩን እንዳከፋው አንስተዋል።

በሙስና እና በሌብነት ተሰማርተው በሚገኙት ላይ ሚወሰደው እርምጃና ተጠያቂነታቸው ቀድሞ ከነበረው ተሻሽሏል ተብሏል። ይህ የተባለው፤ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የስራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ጉባኤውን ባካሄደበት ወቅት ነው።

ፀረ – ሙስና

# ለኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ሥርዓት (ICSMIS) ዙሪያ ሥልጠና ተሰጠ





ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ሥርዓት (ICSMIS) ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል። የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የማኑዋል አሠራርን አስቀርቶ ዘመናዊ የሰው ሀብት አስተዳደር ሥርዓትን ለመከተል ባሠራው ሲስተም ዙሪያ ለተቋማት አመራርና ሠራተኞች እየሰጠ የሚገኘውን ሥልጠና ለኮሚሽኑ ሠራተኞችም ተሰጥቷል።

ከዚህ በኋላ ማንኛውም በሰው ሀብት በኩል የሚሰጡ አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ በሲስተሙ አማካኝነት ብቻ እንደሚሆን የኮሚሽኑ የኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ ተናግረዋል። ይህ ሥርዓት የሰው ሀብት መረጃን ዲጂታላይዝ ከማድረግ ባለፈ በሰው ሀብት ዙሪያ የሚከሰቱ ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል እንደሚያግዝ ተጠቁሟል። ሥልጠናው በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የሲስተም ባለሙያ በሆኑት በአቶ ይልቃል ፀሐይ አማካኝነት የንድፈ-ሀሳብና የተግባር ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ከሥልጠናው ተሳታፊዎች በሲስተሙ አጠቃቀም እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ ጥያቄዎች ተነስተዋል። በተነሱት ጥያቄዎች ላይም በባለሙያው በቂ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

# ስልጠናዎች ወደ ስራ ሲወርዱ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንደሆነ ተገለጸ






የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ከፍተኛ አመራሮች "የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፣ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ" በሚል መሪ ቃል ስልጠና ወስደዋል። ስልጠናው በዋናነት አመራሩ በተቋማዊ አሰራር ውስጥ የሥነ-ምግባር መርሆችን እንዲያከብርና ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን እንዲከላከል ለማስቻል ያለመ ነው።

በስልጠናው መክፈቻ ላይ ንግግር ያደረጉት የድርጅቱ የሰው ሀብት አስተዳደር መመሪያ ስራ አስኪያጅ ወ/ሮ ሠርካለም ዳምጠው፣ ድርጅቱ መሰል ስልጠናዎችን በተደጋጋሚ ሲያዘጋጅ መቆየቱን አስታውሰዋል። ይሁን እንጂ የዚህ ስልጠና ዋነኛ ግብ እውቀትን ከመቅሰም ባለፈ፣ የተገኘውን ትምህርት ወደ ተግባር በመቀየር በተጨባጭ የሥራ ሂደት ላይ ለውጥ ማምጣት እንደሆነ አሳስበዋል። ስራ አስኪያጇ አክለውም "የምንወደውን ህዝብና ሀገርን ከሙስና ነጻ ሆነን ማገልገል ይገባናል" ሲሉ የአመራሩን ታላቅ ኃላፊነት አፅንኦት ሰጥተዋል።

በዶ/ር ዮሐንስ ፔጥሮስ አማካኝነት የተሰጠው ይህ ስልጠና በሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ያተኮረ ነበር። የመጀመሪያው ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሲሆን፣ አመራሮች በሥራ አጋጣሚ ፈታኝ የሆኑ የውሳኔ ሁኔታዎች ሲገጥሟቸው እንዴት በብልሃትና በታማኝነት መወጣት እንዳለባቸው የሚያስረዳ ነው። ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ የጥቅም ግጭት መከላከል ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ የግልና የድርጅት ጥቅሞች በሚጋጩበት ወቅት ተቋማዊ ታማኝነትን ማስጠበቅ በሚቻልባቸው መንገዶች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

የስልጠናው ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየት ለውሳኔ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙ በመረጃ መደገፍና ፍትሐዊ መሆን ለችግሮቹ ተገቢውን መፍትሔ ለመስጠት ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል።

# በሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች እና ፖሊስ ሙስናን በመከላከል ረገድ በሚኖረው ሚና ላይ ትኩረት ያደረገ ስልጠና መሰጠቱ ተገለጸ





የድሬዳዋ አስተዳደር የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የወንጀል መከላከል የሥነ-ምግባር ኃላፊዎችና የፖሊስ አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጥቷል። ስልጠናው በዋናነት በሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች እና ፖሊስ ሙስናን በመከላከል ረገድ በሚኖረው ሚና ዙሪያ ያተኮረ ነው።

በስልጠናው መድረክ ላይ ንግግር ያደረጉት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር አቶ ፌኑስ አብዱልጀባር ጠንካራ ተቋምን ለመገንባት ጠንካራ መሪ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ ሀገርን ወደፊት ለማራመድ ከሙስና የፀዳ አሰራር ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል። በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶች እና በሕዝባዊ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ አመራሮችና ሠራተኞች በመልካም ሥነ-ምግባር ታንጸው፣ ህብረተሰቡን በታማኝነት ማገልገል እንዳለባቸው አጽንኦት ሰጥተዋል።

ኮሚሽነሩ አክለውም ሀገር ወዳድ የፖሊስ አባላትን በመፍጠር ረገድ ትልቅ ሥራ መሥራት እንደሚገባ ገልፀው፣ ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት በመከላከል እና ከተፈጸመም በኋላ በፍጥነት ምላሽ በመስጠት ረገድ አባላቱ በዘመናዊ አሰራር ታግዘው እንዲሰሩ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በመድረኩ ማጠቃለያ ላይ፣ የህዝብ አደራን ያለአግባብ መጠቀም በሕግ ከማስጠየቅ ባለፈ ሀገርን የሚጎዳ ተግባር መሆኑ ተገልጿል። የፖሊስ አባላት ለሥነ-ምግባር ተገዥ በመሆን፣ በቅንነት እና በፍትሃዊነት ዜጎችን ማገልገል እንደሚገባቸው ተመላክቷል።

# የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሕጋዊ ግዴታ ብቻ ሳይሆን የተቋሙ መለያና ዋና መሠረት ነው - አቶ ፀሐይ ሽፈራው,






ሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሕጋዊ ግዴታ ብቻ ሳይሆን የተቋሙ መለያ፣ የተቋሙ ዋና መሠረትና ምሰሶ፣ የሥራ ባህል መሠረት፣ የአመራር ጥራት መገለጫ፣ ቀጣይነት ያለው የዕድገት መሰላል ነው ሲሉ የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው ገለጹ:: ዋና ሥራ አስፈጻሚው ይህንን የተናገሩት የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከአዋሽ ባንክ ጋር በመተባበር «የከፍተኛ አመራሩ አርአያነት ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ» በሚል መሪ ቃል ለባንኩ ማናጅመንት አባላት በሥነ-ምግባራዊ የውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር ዙሪያ በተዘጋጀው የሥልጠና መድረክ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት ነው::

የመልካም አስተዳደር ጥንካሬ በዘመናዊ የባንክ ኢንዱስትሪ የተወዳዳሪነት አይተኬ ሚና እንዳለው ባንካችን በፅኑ ያምናል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ ጠንካራ የኦዲት አሰራርን፣ የተጠያቂነትን እና የታማኝነት እሴትን ተግባራዊ በማድረግ በትጋት ይሰራል፤ እነዚህን የሥነ-ምግባር እሴቶች ለማጎልበት ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን በማውጣትና በማሻሻል እየሰራ እንደሚገኝ አረጋግጠዋል:: ለአብነትም የቦርድና የከፍተኛ ኃላፊዎች የሥነ-ምግባር መመሪያ፣ የሠራተኞች የሥነ-ምግባር መመሪያ፣ የጥቅም ግጭት መከላከልና የጉቦና የሙስና አስተዳደራዊ ፖሊሲ፣ የጥቆማ አቅራቢዎች የበቀል ጥበቃ ፖሊሲ ይገኙበታል ብለዋል::

አክለውም ባንኩ ከኮሚሽኑ ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ የሀብት ምዝገባ ሥርዓት (Ethiopian Asset Registration System - EARS) አማካኝነት ከ7,500 በላይ ሠራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ተደርጓል:: ይህ እንቅስቃሴ በባንካችን ውስጥ የሕግ ተገዥነትን፣ የሥራ ታማኝነትን፣ የሙያ ሥነ-ምግባርን እና የተቋሙን የሥራ ባህል ጥንካሬ ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተናግረዋል:: ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ እንዲዳብር፣ የጥቅም ግጭትን በመከላከል እና ሙስናን እየተከታተሉ እርምጃ በመውሰድ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ብለዋል:: ይህ ሥልጠና የጥቅም ግጭትን አስቀድሞ ለመከላከል፣ የተቋሙን ታማኝነት ለማሳደግ፣ የአመራር ቁርጠኝነትን ለማጎልበት እና ሁሉም የሥራ ዘርፎች ሊተገብሩት የሚገባቸውን የሥነ-ምግባር እሴቶች ለማዳበር የሚያስችል ነው በማለት ሐሳባቸውን ቋጭተዋል::

በኮሚሽኑ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈጻሚዎች ማስተባበሪያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ ፈርዳ ገመዳ በበኩላቸው፣ አዋሽ ባንክ አንጋፋና ትርፋማ ባንክ በመሆኑ በፋይናንሱ ዘርፍ ለሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ሲሉ ገልጸዋል:: መሪ ሥራ አስፈጻሚው አያይዘውም የባንኩ ትርፋማነት ዋናው ምስጢር ደግሞ ታማኝነት ነው:: ስለሆነም ሁሉም አመራር በሙስና መከላከል ላይ እንደ አዋሽ ባንክ ትኩረት አድርጎ መስራት እንዳለበት በመንግሥት ይታመናል ብለዋል::

አክለውም ይህ የከፍተኛ አመራሮች ሥልጠና የጀመረው ለሀገሪቱ የሕግ አውጪ አካል ማለትም ለምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና አባላት በመስጠት ሲሆን፣ ቀጥሎም ለአስፈጻሚው አካል ማለትም ለ27 ዘርፎች ከፍተኛ አመራሮች እየተሰጠ ይገኛል ብለዋል:: የሥልጠና ሞጁሉም ሲዘጋጅ ኮሚሽኑ በዘርፎች ላይ ያካሄደውን የጥናት ግኝት መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ ያዘጋጁትም ከሀገሪቱ ነባር ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ምሁራን መሆናቸውን እና ሥልጠናውንም እነሱ እንዲሰጡ በተወሰነው መሠረት ነው ብለዋል::

ሥልጠናውን የሰጡት ዶ/ር ተስፋዬ ሄርጳሳ በበኩላቸው፣ የሥልጠናው ዋና ዓላማ ዕውቀትን፣ ክህሎትን እና አመለካከትን ለመገንባት ሲሆን፣ በሂደትም ሙስናን ለመከላከል ያለመ ነው ብለዋል:: ዶ/ር ተስፋዬ ሥልጠናውን ከባንክ አሰራር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ኬዞች እያነሱ፣ የዘርፉን የጥቅም ግጭት ተጋላጭነት በማመላከት እንዲሁም እንዴት መከላከል እንደሚቻል ጭምር በመጠቆም በዝርዝር አስረድተዋል:: በመጨረሻም የሥልጠናው ተሳታፊዎች የሥልጠናውን አስፈላጊነት በመግለጽ የተለያዩ ጥያቄዎችን እና አስተያየቶችን ያነሱ ሲሆን፣ ለተነሱት ጥያቄዎችም በአሰልጣኙ በቂ መልስና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸውል::

# ኮርፖሬሽኑ በአመራሩ ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና በጥቅም ግጭት አያያዝ ዙሪያ ያተኮረ ስልጠና ሰጠ







የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ለአመራሩ "የሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭት ማስተዳደር ርዕሰ ጉዳይ፤ የአመራሩ አርዓያነት ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ" በሚል መሪ ቃል በኢትዮጵያ ሆቴል ስልጠና ሰጥቷል::

በመድረኩ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሀይለብርሃን ዜና እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት ኮርፖሬሽኑ በከፍተኛ የእድገት ጎዳና ላይ ይገኛል:: ይህ ተቋማዊ እድገት ደግሞ ሰፊና ውስብስብ የቢዝነስ ስራዎችን የሚያካትት በመሆኑ፣ የአመራሩንና የሰራተኛውን አቅም በየጊዜው መገንባትና መሰል ስልጠናዎችን መስጠት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል:: በተግባር ላይ ያልዋለ እውቀት ለውጥ ማምጣት እንደማይችል በመግለጽ፣ ሰልጣኞች ያገኙትን ግንዛቤ በቀጥታ ወደ ስራ ማምጣት እንዳለባቸውና መሰል የአቅም ግንባታ ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አሳስበዋል::

የመድረኩ አሰልጣኝ ዶ/ር ተስፋዬ ጄርጳሳ በበኩላቸው፣ በተቋማዊ የስራ ሂደት ውስጥ አንዳንድ ጊዜ እሴቶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑበት አጋጣሚ ሊፈጠር እንደሚችል አብራርተዋል:: በዚህ ወቅት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ መልካም አማራጮች መካከል ተገቢውን ምርጫ ለማድረግ "ሥነምግባራዊ አመራር" ወሳኝ መሆኑን ገልጸው፤ ምርጫዎች ሁልጊዜም ቢሆን ህጋዊ መስመርን የተከተሉ መሆን እንዳለባቸው አስገንዝበዋል:: አሰልጣኙ አክለውም የሀብት ምዝገባ የጥቅም ግጭትን አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል ዋነኛ መሳሪያ በመሆኑ፣ ሁሉም አካላት የተጣለባቸውን ሀገራዊና ተቋማዊ ግዴታ ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል::

ከተሳታፊዎች ሰፊ ውይይትና ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆን፣ በተለይም ውል የፈረሙ የቤቶቹ ተጠቃሚዎች ወደ ውጭ ሀገር በሚሄዱበት ወቅት "ሰብዓዊነትን ከህግ አሰራር ጋር ለማስታረቅ" የሚደረገው ጥረት የሚፈጥረው የሥነምግባር አጣብቂኝ አንዱ ማሳያ ሆኖ ተነስቷል:: በተጨማሪም ሙስና የአንድ ተቋም ስጋት ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ቤት የሚገባ ማህበራዊ ጠንቅ በመሆኑ፣ እንደ ማህበረሰብ ሥነምግባርን መገንባት ከተቻለ ሙስናን በቀላሉ ማስተዳደር እንደሚቻል ተገልጿል:: ሆኖም በአሁኑ ወቅት በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ላይ የሚታየው መሸርሸር አሳሳቢ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተሳታፊዎች ጠቁመዋል::

# ወጋገን ባንክ ለአመራሮቹ በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ሰጠ

ወጋገን ባንክ “የአመራሩ አርዓያነት፤ ለፀረ-ሙስና ያለው ፋይዳ!” በሚል መሪ ቃል ለከፍተኛ አመራሮቹ በዋናው መሥሪያ ቤት ሥልጠና መስጠቱን አስታውቋል። ሥልጠናው በዋናነት “ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭትን መከላከልና ማስተዳደር” በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው።

በሥልጠናው መክፈቻ ላይ የባንኩ ቺፍ ሂውማን ካፒታልና የሥራ አስፈጻሚው ተወካይ አቶ ኃይሌ ገብረእግዚአብሔር እንደገለጹት፤ እንዲህ ዓይነት ሥልጠናዎች አመራሩ በዕውቀት እንዲታነጽ ከማድረጋቸውም በላይ፣ የተገኘውን ዕውቀት በተግባር ላይ በማዋል የባንኩን አገልግሎት ማሳደግ ይገባል ብለዋል። የሥልጠናው ዋና ዓላማ የአመራሩን ግንዛቤ በማሳደግ በባንኩ ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሠራር እንዲጠናከር ማድረግ እንደሆነ ተገልጿል።

የኮሚሽኑ ተወካይ አቶ ፈርዳ ገመዳ በበኩላቸው ባስተላለፉት መልዕክት፣ የአመራሩ አርዓያነት ከላይ ወደ ታች የሚወርድ ግልጽ አሠራርን ለመፍጠር ቁልፍ ሚና እንዳለው ገልጸው፤ ይህም እንደ ሀገር የሚሰጡ ስልጠናዎች አካል መሆኑን ጠቁመዋል። ሥልጠናውን የሰጡት ዶ/ር ታደሰ ወልደሰንበት፤ ዕውቀት በየጊዜው የሚሻሻል በመሆኑ አመራሩ ውሳኔዎችን ሲያስተላልፍ የባንኩን የረጅም ጊዜ ፍላጎትና ቀጣይነት ባረጋገጠ መልኩ መሆን እንዳለበት አሳስበዋል።

ከተሳታፊዎች በኩል በሥልጠናው ወቅት እንደተነሳው፤ ባንኩ በተለይ በቴክኖሎጂ ግዥ ወቅት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚያፈስ በመሆኑ፣ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚደረጉ ውሳኔዎች ጥብቅ ሥነ-ምግባርን የተከተሉ ሊሆኑ እንደሚገባ ተመልክቷል። በተጨማሪም በፖሊሲ ቀረጻና በሥራ አፈጻጸም ወቅት የጥቅም ግጭቶችን በጥንቃቄ ማስተዳደር ለተቋሙ ስኬት ወሳኝ መሆኑ በሥልጠናው ላይ በስፋት ተመክሮበታል። አመራሮቹ ለሥልጠናው በሰጡት ከፍተኛ ትኩረት ምስጋና የቀረበ ሲሆን፤ ሥልጠናውም መልካም ተሞክሮዎችን ለማጋራትና የባንኩን የወደፊት ጉዞ ለማሳመር ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ተገልጾ ተጠናቋል።

## ለኢንሹራንስ ኩባንያዎች በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከል ላይ ያተኮረ ሥልጠና ተሰጥቷል





የፌደራል ሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ ”የከፍተኛ አመራሩ አርአያነት ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ” በሚል መሪ ቃል በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከል ላይ ያተኮረ ሥልጠና ለኢንሹራንስ ኩባንያዎች ከፍተኛ አመራሮች ሰጥቷል። በመድረኩ ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ዶ/ር ያሬድ ሞላ፣ ይህ የከፍተኛ አመራሮች ሥልጠና በሥነ-ምግባራዊ የውሳኔ አሰጣጥ እና በጥቅም ግጭት መከላከል ላይ ማተኮሩ በጣም ጠቃሚ ያደርገዋል ብለዋል። አመራሩ ሥልጠናውን በጥሞና ተከታትሎ ከሥልጠናው ያገኘውን ዕውቀት ወደየተቋማቱ በማውረድ በተግባር ላይ ማዋል እንዳለበት አሳስበዋል።

የፌደራል ሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የፀረ-ሙስና ሕዝብ ግንዛቤ ማጎልበቻ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዓለማየሁ ዘሪሁን በበኩላቸው፣ ሙስናን የመከላከል ሥራን የማስተባበር ድርሻ የኮሚሽኑ ቢሆንም ሥራው በአንድ ተቋም ብቻ የሚተው ባለመሆኑ ተቋማት የጉዳዩን አሳሳቢነት ተረድተው በባለቤትነት ሊመሩት ይገባል ብለዋል። አያይዘውም የዚህ ሥልጠና ዋና ዓላማ ተቋማት ሙስናን መከላከል የሚያስችላቸውን አቅም እንዲገነቡና አመራሩ ሥነ-ምግባራዊ ሆኖ እንዲወስን ማስቻል መሆኑን ገልጸዋል። የጥቅም ግጭትን አስቀድሞ መከላከል ጊዜን፣ ገንዘብንና የሥራ ሀብትን ይቆጥባል ሲሉም አክለዋል።

ይህ የከፍተኛ አመራር ሥልጠና ከምክር ቤት አባላት ጀምሮ የተሰጠ ሲሆን፣ የሥልጠና ሞጁሉም የሙስና ተጋላጭ አካባቢዎችን በጥናት በመለየትና በዚያው በጥናቱ የተለዩ ክፍተቶችን መሙላት በሚያስችል መልኩ ተቃኝቶ የተዘጋጀ መሆኑን መሪ ሥራ አስፈጻሚው ገልጸዋል። ሙስናን በመከላከል ረገድ ዲጂታል አሠራርን መከተል እንደ አንድ አማራጭ ሊያገለግል ቢችልም ብቸኛ መፍትሔ ግን አይደለም ብለዋል። ምክንያቱም በሥነ-ምግባር የተቃኘ አመራርና ሠራተኛ መፍጠር ካልተቻለ ጥፋቱም በዚያው ልክ የከፋ ይሆናል። ዕውቀት ኖሮት ሥነ-ምግባር ከጎደለው ሠራተኛ ይልቅ፣ መካከለኛ ዕውቀት ኖሮት መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ሠራተኛ ለሀገር ይበልጥ ይጠቅማል ሲሉም አክለዋል።

ተቋማት ሙስናን ለመከላከል ከመከታተያ ክፍሎች ጋር ተናበውና ተቀናጅተው መሥራት ያስፈልጋል ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ በተለይ አራቱ የሥራ ክፍሎች ማለትም የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል፣ ሕግ፣ ለውጥ እና ኦዲት ተቀናጅተው እንዲሠሩ መመሪያው የሚያዝ ሲሆን አሠራሩም እንደሚፈቅድ አስረድተዋል። ይህንን ቅንጅታዊ አሠራር ደግሞ የበለጠ ውጤታማ የሚያደርገው ከፍተኛ አመራሩ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በኃላፊነት ስሜት ሲመራው መሆኑን ጭምር አብራርተዋል።

## ሙስናን መከላከል የሀገርን ህልውና ማስቀጠል መሆኑ ተገለጸ






አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ ተቋሙን ከሙስና ነጻ ለማድረግና የአመራሩን የአርአያነት ሚና ለማጠናከር ያለመ ስልጠና ላይ የባንኩ ከፍተኛ አመራሮች የተሳተፉ ሲሆን፣ “የአመራሩ አርዓያነት ለፀረ ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ” በሚል መሪ ቃል በስነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና በጥቅም ግጭት አያያዝ ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

የባንኩ ፕሬዜዳንት አቶ ሀይሉ አለሙ በመድረኩ ላይ ባደረጉት ንግግር፣ ሙስና ለአህጉሪቱ እድገት ትልቁ ጋሬጣ መሆኑን ገልጸዋል። አፍሪካ የተፈጥሮ ሀብት ሳያንሳት ነገር ግን በሙስና ምክንያት ሀብቷ ወደ ውጭ እየሸሸ ለሌሎች እንደሚተርፍ ጠቁመው፣ “ሙስና ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የመተላለፍ አቅሙ ከፍተኛ በመሆኑ፣ ሀገር እንደ ሀገር እንድትቀጥል ስጋቱን ቀድሞ መከላከል ይገባል” ብለዋል። ባንኩም የህዝብንና የሀገርን ጥቅም ለማስከበር ሙስናን የመከላከል ፅኑ አቋም እንዳለው አረጋግጠዋል።

በአሰልጣኝ ዶ/ር ታደስ ወልደሰንበት አማካኝነት ስልጠና ተሰጥቷል። የስነ-ምግባር አጣብቂኝ ሲገጥም አመራሮች ውሳኔ በሚሰጡበት ወቅት ሊገጥሟቸው የሚችሉ ዋና ዋና አጣብቂኞች ተለይተው ቀርበዋል፦እውነትን ከፍትሃዊነት ጋር ማመጣጠን፣ ፍትህን ከይቅርታ (ምህረት) ጋር ማዛመድ፣ የግለሰብን ጥቅም ከማህበረሰቡ (ከተቋሙ) ጥቅም ጋር ማስተያየት፣ የአጭር ጊዜ ጥቅምን ከረጅም ጊዜ ስትራቴጂያዊ ግብ ጋር ማመጣጠን ሲገጥም ስነምግባራዊ ውሳኔ አስፈላጊ መሆኑ ቀርቧል። የጥቅም ግጭት አያያዝ በተመለከተ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶች በሦስት ተከፍለው ቀርበዋል። ተጨባጭ፣ ተጋላጭ እና ተገማች ሲሆኑ፤ ባንኩ የጥቅም ግጭት ሲያጋጥም አመራሩ ራሱን ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ማግለል እንዳለበት የሚያዝ ግልጽ ፖሊሲ እንዳለው ተመላክቷል።

የመድረኩ ተሳታፊዎች በባንኩ የሥራ ሂደት ውስጥ በተለይም በግዥና ጨረታ ወቅት ከአቅራቢዎች ሊገጥሙ የሚችሉ አስገዳጅ ሁኔታዎችን እና የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት በአብነት አንስተው ተወያይተዋል። ባንኩ የሚንቀሳቀሰው በህዝብ ገንዘብ በመሆኑ፣ ማንኛውም ውሳኔ የህዝብን አመኔታ ያተረፈ፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነትን የተላበሰ መሆን እንዳለበት ስምምነት ላይ ተደርሷል።

# በባንክ ውስጥ ታማኝነት ከእሴት በፊት ያለ ግዴታ መሆኑ ተገለጸ

ቡና ባንክ ከፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በጋራ በመተባበር “ስነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት ማስተዳደር” በሚል ርዕስ ለቡና ባንክ ከፍተኛ አመራሮች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ የቡና ባንክ ፕሬዜዳንት አቶ ሙሉጌታ አለማየሁ በስልጠናው መክፈቻ ላይ እንደገለጹት፤ ታማኝነት በባንክ ስራ ውስጥ እንደ አንድ የሀብት አይነት ብቻ የሚታይ ሳይሆን፣ ከማንኛውም እሴት በፊት ሊቀደም የሚገባ የሙያ ግዴታ ነው፡፡

“በአሁኑ ወቅት በአቋራጭ መበልጸግ ለትውልዱ ትልቅ ፈተና እየሆነ ነው” ያሉት ፕሬዜዳንቱ፣ ይህንን ለመመከት ስነ-ምግባርን ከልጅነት ጀምሮ በትምህርት መገንባት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ ባንኩ ከሙስና ጋር በተያያዘ “ዜሮ ቶለራንስ” ወይም በፍጹም የማይታገስ መመሪያ እንደሚከተል የገለጹት አቶ ሙሉጌታ፤ “ከመልካም ሽቶ መልካም ስም ይበልጣል እንደሚባለው፣ እኛም እንደ ባንክ ስማችንና ገጽታችን በክፉ እንዲነሳ አንፈልግም” ብለዋል፡፡

የኮሚሽኑ የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ሥልጠና ዴስክ ኃላፊ አቶ ፍቃዱ ባረና በበኩላቸው፣ ኮሚሽኑ ከሚሰራቸው ዋና ዋና ተግባራት አንዱ የስነ-ምግባር ግንባታ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ ስልጠና በአመራሩ ላይ ትኩረት ማድረጉ ልዩ እንደሚያደርገው ገልጸዋል፡፡

ስልጠናው ከዩኒቨርስቲ በመጡ ምሁራን ታግዞ በተቀረጸ ሰነድ እየተሰጠ መሆኑንና በቀጣይም ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

አሰልጣኙ ዶ/ር ዮሐንስ ጴጥሮስ በበኩላቸው፣ የፋይናንስ ዘርፉ በሙስና የሚመጣ ሀብት በስፋት ሊንቀሳቀስበት የሚችል በመሆኑ፣ በዚህ ዘርፍ ላይ ያሉ አመራሮች የሀብት የማዘዝ አቅማቸውን ለፍትሃዊ ውሳኔ ሊጠቀሙበት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ “ሙስና ስነፎች ሳይለፉ የሚመዘብሩበትን ስርዓት በመፍጠር ፍትሃዊነትን ያዛባል” ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በስልጠናው ማጠቃለያ ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን፣ አመራሩ የተቋሙን ገጽታ በመጠበቅ ለበታች ሰራተኞች አርአያ መሆን እንዳለበት በማሳሰብ ስልጠናው ተጠናቋል፡፡

ቡና ባንክ
BUNNA BANK
Bank of the Visionaries!
የባለራዕዮች ባንክ!

# ሕብረት ባንክ ለከፍተኛ አመራሮቹ በስነ-ምግባርና ሙስና መከላከል ዙሪያ ስልጠና ሰጠ

ሕብረት ባንክ “የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት ለፀረ ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ” በሚል መሪ ቃል ለከፍተኛ አመራሮቹ ያዘጋጀውን የአቅም ግንባታ ስልጠና በስኬት ማጠናቀቁን አስታውቋል፡፡ ስልጠናው በዋናነት በስነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሠጣጥ እና የጥቅም ግጭትን በማስወገድ ረገድ የአመራሩን ሚና ለማጠናከር ያለመ ነው፡፡

በስልጠናው መክፈቻ ላይ የተገኙት የሕብረት ባንክ ፕሬዝዳንት አቶ ንጉሱ ገ/አምላክ እንደገለጹት፣ ይህ የስልጠና መርሃ ግብር እንደ ሀገር ሲሰራበት የቆየና በተጨባጭም ለውጥ እያመጣ ያለ ተግባር ነው፡፡ ፕሬዝዳንቱ አክለውም የባንክ ስራ መሰረቱ “እምነት” መሆኑን ጠቅሰው፣ ማህበረሰቡ ባንኩን የሚመርጠው በስነ-ምግባርና በታማኝነት ይሰራል ብሎ በሚጥልበት እምነት መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ “የስልጠናው ዋና አላማ ያለንን ጥንካሬ ይበልጥ ማሳደግ እና ክፍተቶቻችንን በመፈተሽ ለተሻለ አሰራር ራሳችንን እንድናዘጋጅ ማድረግ ነው” ብለዋል፡ ፡ የስልጠናው አቅራቢ ዶ/ር ዘውዱ ዛኬ በበኩላቸው፣ የአንድ አመራር ብቃትና ጥንካሬ የሚመዘነው የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ስነ-ምግባራዊ መሆን መቻላቸውን ተመልክቶ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይ ሰፊ ውይይት ያደረጉት ከፍተኛ አመራሮቹ፣ በባንኩ ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚቻልባቸው መንገዶች ላይ ተወያይተዋል፡፡ በተለይም በጨረታ እና በግዥ ሂደቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግና የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ማስወገድ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ተሳታፊዎቹ በውይይቱ ወቅት እንዳነሱት፣ የሰው ኃይል ቅጥርን በተመለከተ የዘመድ አዝማድ አሰራርን የሚከላከል ስርአት መዘርጋቱንና በግዥ ወቅትም “የእከክልኝ ልከክልህ” አይነት ድብቅ ስምምነቶች እንዳይኖሩ በንቃት መጠበቅ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ በማጠቃለያውም፣ ማንኛውም የባንኩ ውሳኔ የተቋሙን የረጅም ጊዜ ግብና ደህንነት ያገናዘበ እንዲሁም የደንበኞችን አመኔታ የሚያጎለብት መሆን እንዳለበት አፅንዖት ተሰጥቶበታል፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993
ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ


ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
EARS


## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች


ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1


NCRS

## ርዕሰ -አንቀፅ

# ተቋማት የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት ተገልጋይ ተኮር አገልግሎት መስጠት ይገባቸዋል!

የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ለዜጎች በእለት ተእለት አኗኗር አስፈላጊና መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች በመንግሥት ተቋማት የሚከናወንበትና ለዜጎች የሚቀርቡ ሥራዎችን ይመለከታል። የመንግሥት ተቋማት ዋነኛ ግብ በሕግ የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር በብቃት በመፈፀምና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዩን ህብረተሰብ እርካታ ማረጋገጥ ነው። ይህም ዜጎች በመንግሥት ላይ ያላቸውን እምነት በማሳደግ መንግሥት በሚነድፋቸው አገራዊ የልማትና የዕድገት አጀንዳዎች ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ እንዲጎለብት ያደርጋል።

መንግስት የተለያዩ ዕቅዶችን በማዘጋጀትና ስልቶችን በመንደፍ በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ጥረት እያደረገ ይገኛል። ጥረቶቹ ከተቋም ተቋም የሚለያዩና የተሻሻሉ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው አሁንም በፌዴራልም ሆነ በክልል ተቋማት ውስጥ የሚታየው የመልካም አስተዳደር ችግር ለነገ ሳይባል ሊፈታ የሚገባው ጉዳይ ነው። አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ተገቢውን አገልገሎት በማይሰጡበት ጊዜ አገልግሎት ፈላጊውን ማህበረሰብ ለእንግልትና እሮሮ የሚዳርግ የመልካም አስተዳደር ችግርን ይፈጥራል። በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰና አገልግሎቱ ለጉቦ፣ ለአድሎአዊ አሠራር፣ ለማጭበርበርና ለምዝበራ በመጋለጥ ላይ ይገኛል። ይህም ዜጎች አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን በገንዘብ እንዲገዙ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን እያስከተለ ይገኛል።

እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍና ውጤታማ ተገልጋይ ተኮር አገልግሎትን ለማረጋገጥ፣ የመንግሥት ተቋማት የአሠራር ሥርዓታቸውን በቴክኖሎጂ በመታገዝ ማዘመንና ግልጽነትን ማስፈን እየሰሩ ቢሆንም ተደራሽ መሆን ይኖርባቸዋል። በተለይም አገልግሎቶችን በዲጂታል አማራጮች ተደራሽ በማድረግ የሰውን ንክኪ መቀነስ ለብልሹ አሠራርና ለሙስና የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን በእጅጉ ያጠባል። ከዚህ ጎን ለጎንም በየደረጃው የሚገኙ የአመራርና የፈፃሚ አካላትን ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ ጥብቅ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት መዘርጋት ይገባል። ዜጎች ስለ መብታቸውና ስለሚገባቸው የአገልግሎት ደረጃ ያላቸውን ግንዛቤ በማሳደግ በነፃነት ቅሬታ የሚያቀርቡበትና ግብረ-መልስ የሚሰጡበት ሥርዓት ሲጠናከር፣ ተቋማዊ አሠራሩ ከግለሰቦች ፍላጎት ወጥቶ በሕግና በሥርዓት ብቻ እንዲመራ በማድረግ የተገልጋዩን እርካታና የመንግሥትን ተዓማኒነት ማረጋገጥ ይቻላል። የአገልግሎት አሰጣጥ ችግርን በመቅረፍ የመንግሥት አገልግሎት ተገልጋይ ተኮር አገልግሎት መስጠት እንደሚገባ ኮሚሽኑ ለአገልግሎት ሰጭዎች ያሳስባል።

# ሳይቃጠል በቅጠል

## የሥነ-ምግባር ስልጠናዎች ሙስናን በመከላከል ረገድ ያላቸው ጠቀሜታ

የሥነ-ምግባር ስልጠናዎች በህዝባዊ እና በመንግስት ተቋማት ውስጥ መሰጠታቸው፣ ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከልና ተቋማዊ ታማኝነትን ለመገንባት ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይህንን አስፈላጊነት በመገንዘብ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የስልጠና ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ አሁንም አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

የእነዚህ ስልጠናዎች ዋና ዋና ጠቀሜታዎች እና ከኮሚሽኑ ተግባራት ጋር ያላቸው ትስስር በሚከተለው መልኩ ሊታይ ይችላል፡፡

በግንዛቤ ላይ የተመሰረተ መከላከል፡ ሙስና ብዙ ጊዜ የሚጀምረው “ጥቅም እና ግጭት” (Conflict of Interest) እንዲሁም ግልጽነት ከጎደላቸው አሰራሮች ነው፡፡ ስልጠናዎች ሰራተኛውና አመራሩ የትኞቹ ድርጊቶች ወደ ሙስና ሊያመሩ እንደሚችሉ ቀድመው እንዲለዩ ይረዳሉ፡፡

ኮሚሽኑ በየተቋማቱ የሚሰጣቸው ስልጠናዎች ትኩረት የሚያደርጉት ሰራተኞች ስለ ሙስና አስከፊነት፣ ስለ ስነ-ምግባር መርሆዎች እና ስለ ሙስና መከላከያ ህጎች በቂ እውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ ላይ ነው፡፡

ተቋማዊ ባህልን መለወጥ፡ ስልጠናዎች በድርጅት ውስጥ “ሙስናን የማይታገስ” (Zero Tolerance) ባህል እንዲሰርጽ ያደርጋሉ፡፡ ግለሰቦች ለሙስና ያላቸው አመለካከት ሲቀየር፣ ተቋሙ ለሙስና የተጋለጠ የመሆን እድሉ ይቀንሳል፡፡

ኮሚሽኑ የመንግስት ተቋማት የራሳቸውን የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች እንዲያደራጁ እና የስነ-ምግባር መኮንኖችን በማሰልጠን ተቋማዊ ሪፎርም እንዲመጣ ይሰራል፡

የጥቅም ግጭትን የመለየት አቅም፡ ብዙ የመንግስት ሰራተኞችና አመራሮች ሳያውቁት በግል ጥቅማቸው እና በህዝባዊ ኃላፊነታቸው መካከል ግጭት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ስልጠናዎች እነዚህን ሁኔታዎች እንዴት ማስተናገድ እንደሚቻል (ለምሳሌ፦ ስጦታዎችን አለመቀበል፣ ለጥቅም ግጭት የሚያስከትሉ ውሳኔዎች ላይ ራስን ማግለል እና የመሳሰሉትን) መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ ኮሚሽኑ በተለይ ከፍተኛ አመራሮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚሰጣቸው ስልጠናዎች፣ ውሳኔ ሰጪዎች በገለልተኝነት እና በሀቀኝነት እንዲሰሩ አቅም ይፈጥራሉ፡፡

የተጠያቂነት እና የግልጽነት መርሆዎችን ማስረጽ፡ ስልጠናዎች ሰራተኞች ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ለህዝብ ተጠያቂ መሆናቸውን እና አሰራራቸውም ግልጽ መሆን እንዳለበት ግንዛቤ ይፈጥራሉ፡፡ ይህም የመረጃ ፍሰትን በማሳለጥ ለሙስና የሚመቹ ወይም ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ያጠፋል፡፡

ህዝባዊ አመኔታን መገንባት፡ በተቋማት ውስጥ የስነ-ምግባር ስልጠና ተሰጥቶ አሰራሮች ሲስተካከሉ፣ ህዝቡ በመንግስት አገልግሎት ላይ ያለው እምነት ይጨምራል፡፡ ይህ ደግሞ ህዝቡ ራሱ ሙስናን በመታገል ረገድ ከኮሚሽኑ ጋር እንዲተባበር ያነሳሳዋል፡፡

በአጠቃላይ፤ ይሄን መሰረት በማድረግ የፌዴራል የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለመንግታዊ፣ ለህዝባዊ ድርጅቶች ለአመራሮችና ሰራተኞች የሚሰጣቸው ስልጠናዎች ከቅጣት ይልቅ ቅድመ-መከላከል ላይ ትኩረት ያደረጉ በመሆናቸው፣ ሀገራዊ የሙስና ስጋትን በመቀነስ ረገድ የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ ስልጠናዎቹ በንድፈ-ሀሳብ ብቻ ሳይወሰኑ በተግባራዊ መመሪያዎች የተደገፉ መሆናቸው ደግሞ ውጤታማነታቸውን ይጨምረዋል፡፡

## ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችንና ግንዛቤ የሚፈጠርበት እንዲሁም ሀገራችን ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቻውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ህጎችና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው::

በመሆኑም ከአርሶ አደር በሬ ገዝተው በሞባይል ባንክ ገንዘብ ያስተላለፉ አስመስለው የማታለል ወንጀል የፈጸሙት ሙህዲን ሙዘሚል እና ኑርሂማድ መካ በእስራት እና በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ የሸገር ከተማ አስተዳደር የሰንዳፋ በኪ ወረዳ ፍርድ ቤት መወሰኑ ተመላክቷል:: የሰንዳፋ በኪ ወረዳ ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾቹ ላይ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 1 እና አንቀጽ 692 ንዑስ ቁጥር 1 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መተላለፋቸውን ጠቅሶ የማታለል ወንጀል ክስ አቅርቦባቸዋል::




በክሱ ላይ እንደተመላከተው፤ ተከሳሾቹ ለራሳቸው ያልተገባ ሀብት ለማግኘት በሕዳር 10 ቀን 2018 ዓ.ም በሰንዳፋ የከብት ገበያ ከግል ተበዳይ አርሶ አደር ግርማ አብራር ወይፈን በሬ ለመግዛት ተስማምተዋል:: ነገር ግን ለበሬው ግዢ መፈጸሚያ በሚል በግለሰቡ የባንክ ሂሳብ ሁለተኛ ተከሳሽ በሞባይል ባንኪንግ 39 ሺህ ብር ያስተላለፈ አስመስለው ሞባይላቸው ላይ የተጻፈ ሀሰተኛ የመልክት ጽሁፍ ለአርሶ አደሩ በማሳየት በሬውን ይዘው መሰወራቸው [illegible] ወዲያው ገንዘቡን ለማውጣት ወደ ባንክ በሄደበት ወቅት ገንዘቡ አለመግባቱን ከባንክ በተሰጠው ማረጋገጫ መሰረት ጉዳዩን ለፖሊስ ያመለከተ ሲሆን፥ የሰንዳፋ ፖሊስ መምሪያ በጥቆማው መነሻ ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል::

በዚህም ወንጀሉ በተፈጸመ ከአንድ ወር በኋላ ተከሳሾቹ በድጋሚ ወደ ሰንዳፋ የከብት ገበያ በመሄድ በሌላ አርሶ አደር ላይ ተመሳሳይ የማታለል ወንጀል ተግባር ሊፈጽሙ ሲንቀሳቀሱ በፖሊስ ክትትል በቁጥጥር ስር ውለው በዐቃቤ ሕግ ክስ ተመስርቶባቸዋል:: ተከሳሾቹ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት ክደው የዕምነት ክህደት ቃላቸውን መስጠታቸውን ተከትሎ ዐቃቤ ሕግ ለወንጀሉ መፈጸም ያስረዳልኛል ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን በችሎት አቅርቧል:: ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን መርምሮ ተከሳሾቹ በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ቢሆንም መከላከል ባለመቻላቸው የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎባቸዋል::

በዚህም ፍርድ ቤቱ ተከሳሾቹ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን ከግምት በማስገባት በቅጣት ማቅለያነት በመያዝ እያንዳንዳቸውን በ2 ዓመት ከ6 ወራት እስራትና በ1 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ መወሰኑን ተዘግቧል::

## መልካም ዜጋ

# በስህተት ወደ ባንክ አካውንቱ የገባውን ገንዘብ ተመላሽ ያደረገው የፖሊስ

በአዲስ አበባ ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሌጅ ዋና መምሪያ መምህር የሆኑት ኮማንደር ኃ/ማርያም በቀለ፣ በአቢሲኒያ ባንክ አካውንታቸው በስህተት የገባውን 77 ሺህ 630 ብር ለባንኩ ተመላሽ በማድረጋቸው በባንኩ ምስጋና ተችሯቸዋል:: ይህን መሰል ሥነ-ምግባራዊ ተግባራት ምንም እንኳን ከአንድ የፖሊስ መኮንን የሚጠበቅ ቢሆንም፣ አመራሩ ላሳዩት መልካም አርዓያነት ያለው ተግባር የአዲስ አበባ ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ ምስጋናውን አቅርቦ በፌስቡክ ገጹ አስታውቋል::



ባንኩም ለኮማንደር ኃይለማሪያም በቀለ የምስጋናና የእውቅና ደብዳቤ የሰጣቸው ሲሆን፣ ተግባራቸው ከፍተኛ የኃላፊነት ስሜትንና ሥነ-ምግባራዊ እሴትን፣ እንዲሁም ለታማኝነትና ለተጠያቂነት መርሆች ያላቸውን ክብር የሚያንጸባርቅ ነው:: እንዲህ አይነቱ ባህሪ እጅግ የሚያስመሰግንና በህብረተሰቡ ውስጥ ለሌሎች አርዓያ የሚሆን ተግባር መሆኑን በደብዳቤው ገልጿል:: የዝግጅት ክፍላችን በሚከተለው መልኩ ሲገልጻቸው፤ ኮማንደር ኃ/ማርያም ተራ የህብረተሰብ ክፍል ብቻ አይደሉም፤ እርሳቸው የህግ አስከባሪዎችን የሚያሰለጥን እና የሚቀርጽ የፖሊስ ኮሌጅ ዋና መምህር ናቸው::

አንድ መምህር በክፍል ውስጥ ስለ ህግ አክባሪነት፣ ስለ ሐቀኝነት እና ስለ ሙያ ስነ-ምግባር በንድፈ-ሀሳብ ሊያስተምር ይችላል:: ኮማንደር ኃ/ማርያም ግን ያስተማሩትን ትምህርት በህይወታቸው በተግባር አሳይተዋል:: “መምህርነት በቃል መናገር ብቻ ሳይሆን በህይወት መመስከር ጭምር ነው” የሚለውን መርህ በተግባር አስመስክረዋል:: ይህ ተግባራቸው በኮሌጁ ለሚሰለጥኑ እጩ ፖሊሶች ከሺህ መጻሕፍት በላይ የሚመዝን ትልቅ የተግባር ትምህርት ነው::

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ እንዲህ ያሉ የሐቀኝነት ተግባራት በዲጂታል የገንዘብ ዝውውር ሥርዓት ውስጥ የሚከሰቱ ስህተቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና የባንኮችን አስተማማኝነት ለማሳደግ ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ:: በመሆኑም እርሳቸው ያሳዩት የላቀ የሞራል ልዕልና በመላው አገሪቱ ለሚገኙ የመንግሥት ሠራተኞችና ወጣቶች ሊከተሉት የሚገባ ዘላቂ አርአያ ነው:: ስለሆነም ሁሉም የእሳቸውን ተምሳሌታዊ ተግባር በመከተል ኃላፊነቱን እንዲወጣ የዝግጅት ክፍላችን መልዕክቱን ያስተላልፋል::

# ኪነ-ጥበብ

## ሥነምግባር

ከእንስሳት ከፍጥረት ከዱር ከአራዊቱ፣
የሚለያይበት መለኪያ መስፈርቱ፡፡
አታድርግ አድርግ የሚልበት፣
ትክክል መሆኑን የሚመዝንበት፣
ትክክል ካልሆነ ለአእምሮው የሚነግረው፣
የሚለያይበት ጥሩውን ከመጥፎው፡፡
ምርጫ የሚሰጠው ከጥሩውም ጥሩ፣
ሥነ-ምግባር አይደል የማወቅ ገቢሩ፡፡
በሥነ-ምግባር ውስጥ ነው የሰው ልጆች
ልጓም፣
እውቀትም ለብቻው ብዙም አያጓጓም፡፡
እናም መጠቅለያው የሁሉም ማሰሪያ፣
የዓለም መዘውሩ የመተዳደሪያ፣
ሥነ-ምግባር አይደል  የዓለም ሁሉ ጣሪያ፡፡
የወሉን የግሉን ምን መሆን እንዳለ፣
ያስቀምጣል ስርዓት እያደላደለ፡፡
እናም በመሆኑ ስነ-ምግባር ጠበቅ፣
ከሁሉም በትኩረት ከፊት በማስቀመጥ፣
ልንይዘው ይገባል በጥልቀት በማወቅ፡፡
መጥፎን ለማሸነፍ ከመልካምም መልካም
ነጥሎ ካሳየን፣
ሁልጊዜም አደራ ምግባራዊ እንሁን፡፡
ከፍቃዱ በላይ